የገመድ ጉተታ



Yvonne Winer

Connie Bull

የገመድ ጉተታ

retold by Yvonne Winer
illustrated by Connie Bull

በአንዲት ትንሽ ደሴት ላይ ጉማሬ፣ ዝሆን እና ጥንቸል ይኖሩ ነበር።

ጉማሬ በደሴቲቱ በአንደኛው ወገን ይኖር ነበር ፣ ዝሆን ደግሞ በሌላኛው ፣ እና ጥንቸል መሃል ላይ በአንድ ኮረብታ ላይ ይኖሩ ነበር።

ጥንቸል ዝሆን እና ጉማሬ ስለረበሹት ተናደደ። ስለዚህ እነሱን ለማታለል ብልህ የሆነ መላ ዘየደ።

አንዳንድ ሃረጎችን አግኝቶ ረጅም ገመድ ለመሥራት በጥንቃቄ አጣሞ ሰራ።

በመጀመሪያ፣ ወደ ዝሆን ሄዶ፣ “ዝሆን፣ ካንተ በጣም ጠንካራ እንደሆንኩ አምናለሁ” አለው።

ዝሆን ሳቀና፣ “ሞኝ ጥንቸል፣ እኔ ካንተ በጣም ትልቅ ነኝ። ስለዚህ የበለጠ ጠንካራ ነኝ ማለት ነው” አለ።

“ይህን ገመድ በዙሪያህ ልሰርና። ወደ ኮረብታው እየተጎተትኩህ መውጣት እንደምችል ላረጋግጥልህ።” አለ ጥንቸል።

ጥንቸል ገመዱን እንዳሰረበት ዝሆን ሳቀ።

"ኮረብታውን የገመዱን ሌላኛው ጫፍ ይዤ እሮጣለሁ" አለ ጥንቸል። "ከላይ ስደርስ 'ጎትት' ብዬ እጮኻለሁ። ያኔ እኔ ከአንተ የበለጠ ጠንካራ እንደሆንኩ ትረዳለህ።

በመቀጠል ጥንቸል ኮረብታው ላይ ሮጦ በሌላኛው በኩል ወደ ጉማሬ ወረደ።



አሁንም “ጉማሬ፣ እኔ ካንተ በጣም ጠንካራ እንደሆንኩ አምናለሁ” አለ ጥንቸሉ።

ጉማሬ ሳቀና፣ “ሞኝ ጥንቸል፣ እኔ ካንተ በጣም እከብዳለሁ። ስለዚህ እኔ በእርግጥ ጠንካራ ነኝ።

“ይህን ገመድ በዙሪያህ ልሰረው። ያኔ ወደ ኮረብታው ልስብህ እንደምችል አረጋግጣለሁ” አለ ጥንቸል።

ጥንቸል ገመዱን በዙሪያው ሲያስረው ጉማሬ ጮክ ብሎ ሳቀ።

"ከገመዱ ሌላኛው ጫፍ በኩል ወደ ኮረብታው እሮጣለሁ" አለ ጥንቸል። "ከላይ ስደርስ 'ጎትት' ብዬ እጮኻለሁ። ያን ጊዜ እኔ ከአንተ የበለጠ ጠንካራ እንደሆንኩ ታውቃለህ።

ጥንቸል ዝሆኑ እና ጉማሬው በኮረብታው አናት ላይ ሊያዩት እንደሚችሉ እንዳወቀ፣ “ጎትት” ብሎ ጮኸ።

የገመድ ጉተታው ተጀመረ!

ዝሆን ጎትቶ ጎትቶ አንገቱን ቀና አደረገ። ጉማሬውን በግማሽ መንገድ ወደ ኮረብታው ጎተተው።

ከዚያም ጉማሬ እያጉረመረመ እና እየታገለ ዝሆንን ግማሹን ኮረብታው ላይ እስኪደርስ ድረስ ጎተተው።

ዝሆን እና ጉማሬ ሁለቱም ሲፋለሙ ጥንቸል ሳቀች።
ከዚያም ስለታም ድንጋይ ወስዶ ገመዱን ለሁለት
በጠሰው።

ጉማሬ እና ዝሆን በትልቅ ግርግር ወደ ባህር ውስጥ ገቡ!

ሁለቱም ጥንቸል በእርግጥም በጣም
ጠንካራ ነው ማለት ነው ብለው አሰቡ።
ከዛ በኋላም ደግመው አላስቸገሩትም።

Era Books